የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፸፯
አዲስ አበባ ነሐሴ ፫ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

25th Year No. 77
ADDIS ABABA 9th August, 2019

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፶./፪ሺ፲፩ ዓ.ም

**የንግድ ምዝገባና ፈቃድ (ማሻሻያ) አዋጅ ….ገጽ…፲፩ሺ፬፻፴፱**

## Content

Proclamation No. 1150/2019

**Commercial Registration and Business Licensing (Amendment) Proclamation..............Page 11439**

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፶/፪ሺ፲፩

## የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት አሰጣጥን ቀላል፣ ቀልጣፋ፣ ወጪ ቆጣቢ፣ ዘመናዊ እና ተደራሽ በማድረግ ለንግድ ሥራ መጀመር ምቹ ሀገር ለመሆን እንዲያስችል የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር ፱፻፹/፪ሺ፰ን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፖብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) መሠረት ይህ ማሻሻያ አዋጅ ታውጇል፡፡

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ “የንግድ ምዝገባና ፈቃድ (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፶/፪ሺ፲፩” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## PROCLAMATION No. 1150/2019

## A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE AMENDMENT OF COMMERCIAL REGISTRATION AND BUSINESS LICENSING

**WHEREAS,** it has become necessary to amend proclamation registration and business licensing No.980/2016 to put in place a commercial registration and business licensing regime that is responsive to the needs of doing business through simple, efficient, modern and accessible registration and licensing services;

**NOW THEREFORE,** in accordance with article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows.

**1. Short Title**

This proclamation may be cited as the “Commercial Registration and Business Licensing (amendment) Proclamation No. 1150/2019”.

## ፪. ማሻሻያ

የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር ፱፻፹/፪ሺ፰ እንደሚከተለው ተሻሽሏል:-

፩/ የአዋጁ አንቀጽ ፪ (፪) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተተክቷል:-

"፪/ "ነጋዴ" ማለት ንግድን የሙያ ሥራው አድርጎ ተገቢውን ጥቅም ለማግኘት በንግድ ሕጉና በኢትዮጵያ የንግድ ሥራ ፈቃድ መስጫ መደብ መመሪያ ውስጥ የተዘረዘሩትን ማንኛውንም ሥራዎች የሚሰራ ሰው ነው፤"

፪/ የአዋጁ አንቀጽ ፪ (፴፬) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፴፬) ተተክቷል:-

"፴፬/ "የኢትዮጵያ የንግድ ሥራ ፈቃድ መስጫ መደብ መመሪያ" ማለት በኢትዮጵያ ውስጥ የንግድ ሥራ ፈቃድ የሚሰጥባቸው የንግድ ሥራዎችን ዓይነትና ዝርዝር መግለጫ የያዘ ሀገር አቀፍ ተፈፃሚነት ያለው በሚኒስቴሩ የሚወጣ መመሪያ ነው፤"

፫/ የአዋጁ አንቀጽ ፪ (፵፬) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፵፬) ተተክቷል:-

"፵፬/"አግባብ ያለው ባለስልጣን" ማለት የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ወይም በክልል ንግድን ለማስተዳደር በሕግ ሥልጣን የተሰጣቸው አካላት ናቸው፤"

፬/ የአዋጁ አንቀጽ ፪ (፵፭) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፵፭) ተተክቷል:-

"፵፭/ "ሚኒስቴር" ወይም "ሚኒስትር" ማለት የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤"



## 2. Amendment

The Commercial Registration and Business Licensing Proclamation No.980/2016 is amended as follows:

1/ article 2 (2) of the proclamation is deleted and replaced by the following new sub article (2):

"2/ "business person" means any person who professionally and for gain carries on any of the activities specified in the commercial code and the Ethiopian Business Licensing Categories."

2/ article 2 (34) of the proclamation is deleted and replaced by the following new sub-article (34)

"34/ "the Ethiopian Business Licensing Categories Directive" means a directive of national application issued by the ministry providing for a list and types of commercial activities for which business licenses are issued in Ethiopia.

3/ article 2 (44) of the proclamation is deleted and replaced by the following new sub-article (44)

"44/ "relevant authority" means Ministry of Trade and Industry or Regional Organs Administering Commercial Activities."

4/ article 2 (45) of the proclamation is deleted and replaced by the following new sub-article( 45)

"45/ "Ministry" or "Minister" means the Ministry of Trade and Industry or the Minister of Trade and Tndustry."

፭/ ከአዋጁ አንቀጽ ፬ (፲፮) ቀጥሎ አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፲፯) ተጨምሯል፤

“፲፯/ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎቶችን የኢንፎርሜሽን መገናኛ ቴክኖሎጂ አውታሮችን በመጠቀም ተገልጋዮች ወደ አገልግሎት ሰጪው በአካል ሳይቀርቡ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ የሚያስችሉ አሰራሮችን እና ሥርዓቶችን በሀገር አቀፍ ደረጃ ይዘረጋል፤ ተፈፃሚ እንዲሆንም ያደርጋል፤”

፮/ የአዋጁ አንቀጽ ፭ (፮) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፮) ተተክቷል፤ ከአዋጁ አንቀጽ ፭ (፱) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፲) ተጨምሯል፤

“፮/ በንግድ ማህበራት መመስረቻ ጽሑፎችና መተዳደርያ ደንቦች እንዲሁም ማሻሻያዎች እና ለውጦቻቸው የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት ሰጪ አካላት ውስጥ በሚቋቋሙ የአንድ ማዕከል አገልግሎት ሰነዶችን ለማረጋገጥ በሕግ ሥልጣን የተሰጠው አካል ሙያተኛ በመመደብ እንዲረጋገጥ ያደርጋል፤”

“፲/ በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት ሰጪ አካላት ውስጥ በሚቋቋሙ የአንድ ማዕከል አገልግሎቶች የግብር ከፋይ መለያ ቁጥርን ለመስጠት በሕግ ሥልጣን የተሰጠው አካል ሙያተኛ በመመደብ ሥራው እንዲሰራ ያደርጋል፤

፯/ የአዋጁ አንቀጽ ፯ (፪) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፳፭) ተተክቷል፤

5/ a new sub-article (17) is added following article 4 (16) of the proclamation;

“17/ the ministry shall put in place and follow up the implementation of systems that will make it possible for service recipients to get registration and licensing services without physically appearing at the registering offices by means of information and communication technology.”

6/ article 5 (6) of the proclamation is deleted and replaced by the following new sub article( 6); a new sub-article (10) is added following article 5 (9) of the proclamation;

“6/ memorandum of associations and articles of associations and any amendments and alterations thereto shall be authenticated by a Professional to be assigned by a government body authorized by law to authenticate documents who will based in one stop shop centers to be set up within the commercial registering and business licensing bodies.”

10/ a body authorized by law to issue tax identification numbers shall assigned a Professional to the one stop shop centers to be set up within the commercial registering and licensing bodies to issue tax identification numbers;

7/ article 7 (2) of the proclamation is deleted and replaced by the following new sub article (2);

“፪/ የግለሰብ ነጋዴ ወይም የንግድ ማህበራት ሲመሰረቱ ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት የምዝገባ የምስክር ወረቀት ለሚሰጣቸው ሰዎች አግባብ ያለው ባለስልጣን ተደራሽ የሆኑ የኢንፎርሜሽን መገናኛ ቴክኖሎጂ አውታሮችን በመጠቀም የምዝገባና ፈቃድ መረጃዎቻቸውን ይፋ ያደርጋል፤”

፰/ የአዋጁ አንቀጽ ፲ (፭) ተሰርዟል፤

፱/ የአዋጁ አንቀጽ ፲ (፩) ተሰርዞ በሚከለተው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተተክቷል:-

“፩/ ማንኛውም የንግድ ምዝገባ ለውጥ ወይም ማሻሻያ በንግድ ሕጉ መሠረት መዘጋጀቱን በማረጋገጥ መዝጋቢው አካል መመዝገብ አለበት፤”

፲/ የአዋጁ አንቀጽ ፲፩ (፩) (ሠ)፣ (፪) እና (፰) ተሰርዘው ከንዑስ አንቀጽ (፫) እስከ (፯) ያሉት እንደቅደም ተከተላቸው ከንዑስ አንቀጽ ፪ እስከ ፯ ሆነው ተሸጋሽገዋል፤

፲፩/ የአዋጁ አንቀጽ ፲፩ (፯) (እንደተሸጋሸገው) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፯) ተተክቷል:-

“፯/ ማንኛውም ኃላፊነቱ የተወሰነ የንግድ ማህበር ምዝገባ ስረዛ የሚፀናው አግባብ ያለው ባለስልጣን ስረዛውን ተደራሽ በሆነ የኢንፎርሜሽን መገናኛ ቴክኖሎጂ አውታርን ተጠቅሞ ካሳወቀበት ከአንድ ወር በኋላ ነው፡፡ የግለሰብ ነጋዴ በሆነ ጊዜ ስረዛው ከተከናወነበት ቀን ጀምሮ እንደተሰረዘ ይቆጠራል፤”

፲፪/ የአዋጁ ክፍል ፫ ርዕስ ስለ “ንግድ ስም’ ምዝገባ የሚለው ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ርዕስ ተተክቷል:-

“2/ where sole proprietorships or business organizations are established,or registration certificates are issued to any person under this proclamation, the relevant authority shall, by means of accessible information communication technology make public information relating to their registration and licensing.”

8/ article 10(5) of the proclamation is deleted;

9/ article 10 (1) of the proclamation is deleted and replaced by the following new sub-article (1)

“1/ the registering office shall before registering ensure any alterations of or a mendment **to** commercial registration are prepared in accordance with the provisions of the commercial code.”

10/ article 11(1) (e) (2) and (8) of the proclamation are deleted and the subsequent sub articles from 3 to 7 re-arrnged as sub articles (2) to (6) respectively;

11/ article 11 (6) of the proclamation (as renumbered) is deleted and replaced by the following new sub article (6).

“6/ cancellation of registration of a private limited company shall only be valid a month after the registering authority made it public by means of accessible communication and information technology. Where the cancellation involves sole proprietorships it shall be valid as from the date of such cancellation.

12/the title of part three of the Proclamation “registration of trade name’ is deleted and replaced by the following new title of part three:

**"የክፍል ሦስት:- ርዕስ "ስለድርጅትና ንግድ ስሞች"**

፲፫/ የአዋጁ አንቀጽ ፲፬ እና ፲፭ ተሰርዘው በሚከተሉት አዲስ አንቀጾች ፲፬ እና ፲፭ ተተክተዋል:-

**"አንቀጽ ፲፬ ርዕስ "ስለደርጅት ስም ምዝገባ"፤"**

**"አንቀጽ ፲፭ ርዕስ "ስለንግድ ስም ምዝገባ"፤**

፲፬/ የአዋጁ አንቀጽ ፲፮ (፩) (ሐ) ተሰርዞ፤ከፊደል ተራ (መ) እስከ (ረ) ያሉት እንደቅደም ተከተላቸው ከፊደል ተራ (ሐ) እስከ (ሠ) ሆነው ተሸጋሽገዋል፤

፲፭/ ከአዋጁ አንቀጽ ፲፮ (፫) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፬) ተጨምሯል፤

"፬/ በዚህ አንቀጽ ስለንግድ ስም የተገለፁት ለድርጅት ስምም ያገለግላሉ፤"

፲፮/ ከአዋጁ አንቀጽ ፳፩ (፭) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፮) ተጨምሯል፤

"፮/ በአዋጁ ወይም በሌሎች ሕጎች ወይም በውክልና ስልጣን የንግድ ሥራ ፈቃድ ተግባራትን የሚያከናውኑ አካላት የንግድ ሥራ ፈቃድ መረጃዎችን ሚኒስቴሩ ለዚህ ዓላማ ላዘጋጀው የመረጃ ቋት የንግድ ሥራ ፈቃዱ እንደተከናወነ ማስተላለፍ አለባቸው፤

፲፯/ የአዋጁ አንቀጽ ፳፯ (፪)፣ (፮) እና (፯) ተሰርዘው በሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጾች(፪)፣ (፮) እና (፯) ተተክተዋል:-

"፪/ ኃላፊነታቸው የተወሰነ የንግድ ማህበራት ካስመዘገቡት ካፒታል ሦስት አራተኛውን እና ከዚያም በላይ የከሰሩ ከሆነ ካፒታላቸው ከአንድ አራተኛ በላይ እንዲሆን በማድረግ ፈቃዳቸውን ማሳደስ ይችላሉ፤"

**Part Three: "Company and Trade Names"**

13/ Article 14 and 15 of the proclamation are deleted and replaced by the following new article 14 and 15:

**"Title of article 14. Registration of Company Names**

**"Title of article 15. Registration of Trade Names"**

14/ article 16 (1) (c) of the proclamation is deleted and the subsequent from paragraph (d) to (f) are rearranged as paragraph (c) to (e) respectively;

15/ a new sub-article (4) is added following article 16 (3) of the proclamation;

"4/ Trade name expressed under this article shall be applicable to company names;"

16/ a new sub-article (6) is added following article 21(5) of the proclamation;

"6/ licensing bodies issuing licenses pursuant to the proclamation or in accordance with other authorizing laws or through delegated powers shall forward information to the ministry's commercial registration data center, prepared for the purpose, immediately after issuing licenses;

17/article 27 (2), (6) and (7) of the proclamation are deleted and replaced by the following new sub-articles (2),(6) and (7):

"2/ Where three fourth or above of the capital of private limited companies are lost, they can raise their capital by more than one fourth and get their licenses renewed.

"፮/ በቅጣት የማደሻ ጊዜ ውስጥ ያላደሰ ማንኛውም ነጋዴ በቅጣት የማደሻው ጊዜ ከተጠናቀቀበት ቀን ጀምሮ ባለው አንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ብር ፳ ሺ. በመክፈል ማደስ ይችላል፤"

"፯/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፮) መሠረት ያልታደሰ ንግድ ፈቃድ እንደተሰረዘ ይቆጠራል፡፡ ሆኖም ያንኑ ፈቃድ መልሶ ማውጣት የሚቻለው በቅጣት የማሳደሻ ጊዜው ከተጠናቀቀበት ቀን ጀምሮ ከአንድ ዓመት በኋላ ያለምንም ተጨማሪ ቅጣት እንደአዲስ መውሰድ ይችላል፤"

"6/ Where a business person has not renewed its business license within the period of renewal under penalty it can renew the license within one year after the end of the period of renewal under penalty upon payment of birr 20,000.

7/ Business license not renewed in accordance with sub-article (6) of this article shall be deemed cancelled. notwithstanding the foregoing, the license under review can be issued without any other penalty as new, provided application is submitted a year after the end of the period for the renewal of licenses."

## ፫. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

## 3. <u>Effective Date</u>

This proclamation shall enter into force on the date of its publication in the Federal negarit gazette.

አዲስ አበባ ነሐሴ ፫ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም

**Done at Addis Ababa, this 9th day of Auguste,2019.**

ሳህለወርቅ ዘውዴ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፓብሊክ ፕሬዘዳንት

**SAHLEWORK ZEWDIE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**